ጉምሩክ ኮሚሽን የመቐለ ቅ/ጽ/ቤት የተለያዩ ያገለገሉ የተሽከረካሪ አካላት እና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ የተለያዩ ያገለገሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እንዲሁም የተለያዩ ያገለገሉ ፕላስቲክ ወንበሮች ባሉበት መሸጥ ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ረቡዕ ጉንበት 26, 2018 (ከ 5 ወር)
- መዝግያ ቀን: ሰነ 11, 2018 4:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:2%
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ሰነ 11, 2018 4:15 ጥዋት
- ምድብ: ካልኦት ዝሸወጡ/ ዘገልገሉ ኣቅሑት መሸጣ/

የጨረታ ማስታወቂያ

ቁጥር 001/2018

የቅ/ጽ/ቤቱ የ2018 በጀት ዓመት፤ የተለያዩ ያገለገሉ የተሽከረካሪ አካላት እና መለዋወጫ ዕቃዎች፤ የተለያዩ ያገለገሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እንዲሁም የተለያዩ ያገለገሉ ፕላስቲክ ወንበሮች ባሉበት የጨረታ ሽያጭ

- ሎት 1. የተለያዩ ያገለገሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ሽያጭ፤
- ሎት 2 የተለያዩ ያገለገሉ የመኪና ጎማ፣ ያገለገሉ ባትሪ እና ያገለገሉ የመኪና ዕቃዎች/ ብረት/ ሽያጭ
- ሎት 3.ያገለገሉና የተሰባበሩ ፕላስቲክ ወንበሮች ሽያጭ

ስለሆነም ተወዳዳሪዎች/ተጫራቾች ፡-

- በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የአቅራቢነት ዝርዝር በዌብሳይት ላይ የተመዘገቡበት ወረቀት (በቅርብ ጊዜ ፕሪንት የተደረገ)፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና ግብር ከሚከፈልበት መ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ የምዝገባ ማስረጃ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል መቐለ ጉምሩክ ኮሚሽን ኤስኤስ ማዞሪያ ቢሮ ቁጥር 301 በመቅረብ መውሰድ ይችላሉ።
- የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 2% ወይም ብር 2,000.00 /ሁለት ሺህ ብር በባንክ በተረጋገጠ CPO ወይም ቢድ ቦንድ /BID BOND/ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አሸገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ተጫራቾች ለሚገዙት ንብረት ባሸነፉት ዕቃ ላይ 10% የውል ማስከበሪያ ዋስትና በስማቸው በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
- በሰነዶቻቸው ላይ ስማቸውን፣ ሙሉ አድራሻቸውንና ፊርማቸውን አሟልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- በተጫራቾች ዋጋ ላይ ተንተርሶ የሚቀርብ ዋጋ ተቀባይነት የለውም።
- አቅራቢዎች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በጨረታ ሰነዱ ላይ በጥንቃቄ በመሙላት በእያንዳንዱ ገፅ ፊርማ እና የድርጅቱን ማህተም በመምታት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በፖስታ ውስጥ አስገብቶ በማሸግ በቅ/ፅ/ቤታችን ስም የጨረታ ቁጥሩን እና የግዥውን አይነት በመግለጽ በኤንቨሎፕ ላይ በመጻፍ ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
- የጨረታ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ የጨረታ ሰነዳቸውን ማስገባት የሚችሉ ሲሆን በዚሁ ቀን 4፡00 ሰአት የጨረታ ሳጥኑ ታሽጎ በ4:15 ተጫራቾች እና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል። ነገር ግን የመክፈቻው ቀን እሁድ ወይም የበአል ቀን ላይ ከዋለ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰአት ታሽጎ ይከፈታል።
- ለአሸናፊ ተወዳዳሪዎች በጨረታው ማሸነፋቸው እንደተገለጸላቸው ቅሬታ ያላቸው ተወዳዳሪዎች ቅሬታቸውን በጽሑፍ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ በ5 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላሉ። በውድድሩ የቀረበ ቅሬታ ከሌለ አሸናፊ ድርጅቶች በ15 ቀናት ውስጥ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ቀርበው ግዥውን ከሚፈፅመው አካል ጋር ውል ይፈፅማሉ።

 መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለበለጠመረጃ ስልክ ቁጥር፡-09 42-60 36 08/ 09 14 75 49 40 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።

አድራሻ፡- በጉምሩክ ኮሚሽን የመቐለ ቅ/ፅ/ቤት ኤስኤስ ማዞሪያ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 301

በጉምሩክ ኮሚሽን የመቐለ ቅ/ጽ/ቤት

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle